# ለእግዚአብሔር ፍቅር

“… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48፥17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 - 9395

ሕዳር 1995 November 2002 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፤ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።” (ኢሳ 54፥13)

---------- አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ -------------

# ሦስት ተረት፥አንድ ታሪክ

## ሦስት ዛፎች

በአንድ ኮረብታ ላይ ባለው ጫካ መሐከል ሦስት ዛፎች ነበሩ። እነርሱም ስለ ወደ ፊት ኑሮአቸውና ምኞታቸው ይወያዩ ነበር። አንደኛው ዛፍ፦ “እኔ በሚገባ ካደግሁ በኋላ፥ቁም ሣጥን መሆን እመኛለሁ።እጅግ በተዋበ አቀራረጽ ተጠርቤ ፥ አምሬ፥ ሰው ሁሉ ውበቴን ለመመልከት የሚጓጓ እሆናለሁ። የመኳንንትና የንግሥቶችም ጌጣ ጌጥ ማኖሪያ እሆናለሁ፡” ሲል ምኞቱን ገለጸ።

* * *

. ከዚያም ምኞታቸውን ለጥቂት ዓመታት ሲጠባበቁ ከቆዩ በኋላ፥ከዕለታት አንድ ቀን ዛፍ ቆራጮች ጥሩ ዛፍ ፍለጋ በጫካው ውስጥ ሲዞሩ ብቅ አሉ። ምን የመሳሰለ መጥረብያ በትክሻቸው አንግተዋል። አንዱ ዛፍ ቆራጭ ወደ መጀመሪያው ዛፍ ጠጋ አለና፥ “ይኸኛው ዛፍ ጠንካራ ይመስላል። አናጢዎች በደስታ ይገዙታል”፥በማለት መጥረብያውን ሳብ አደረገና መቁረጥ ጀመረ። ዛፉም (መቆረጥ ደስ ባይልም) ከዚያ ባሻገር ያለውን የምኞቱን መፈጸም፥በሩቅ አያስተዋለ ታገሰ። “መጀመሪያ እቆረጣለሁ፥ከዚያም በአናጢ እጅ ተገዝግዤ፥ ተቆርጬና ተጠርቤ፥ መከራዬን ከጨረስኩ በኋላ ቁም ሣጥን እሆናለሁ” አለ። እንዳለውም ጨክኖ ታገሰና ተቆርጦ ወደቀ።

* * *

የመጀመሪያው ዛፍ አናጢ ፊት ቀረበ። አናጢውም ተቀብሎ የእንስሳት መመገብያ ገበታ አድርጎ ሠራው። ከዚያም ወስዶ በከብቶች በረት ውስጥ አስቀመጠና በከብቶች መኖ ሞላው። ከብቶቹም ከገበታው ተመገቡ። በዚህን ጊዜ ዛፉ ደነገጠ፡አዘነ፤ “የህ እኮ ጸሎቴ አይደለም። እንዲህ ያለ አገልግሎት በፍጹም አስቤ አላውቅም።” ያሳዝናል፡ እያለ ወተወተ።

* * *

ይህ በእንዲህ እያለ፥ከዕለታት አንድ ቀን፥አንድ ሰው ለመውለድ ከተቃረበች ሴት ጋር ሲጓዝ፥ማረፍያ ያስፈልጋቸው ነበር። ማረፊያም ስላልተገኘ፡በበረቱ ውስጥ ለማረፍ ተገደዱ፤ ከዚያም ሴቲቱን ምጥ ያዛትና ወንድ ልጅ ወለደች።ያም ከዛፉ የተሠራው ገበታ በበረቱ ውስጥ ከነበሩት ሁሉ የተሻለ ሥፍራ ስለ ነበረ፥ልጁን በዚያ ላይ አኖሩት ገበታውም ወዲያው የተለየ ስሜት ተሰማው። ማስተዋልም ጀመረ። ሕፃኑ ኢየሱስ ነበረ። ሁኔታውም ድንቅ መሆኑን ተገነዘበ። ከሁሉ የከበረውን ሕፃን ኢየሱስን በማዘሉ፥ ከተመኘው ይበልጥ እንደ ተፈጸመለት አስተዋለ ። እግዚአብሔርንም አመሰገነ።



. ቀጥሎ ሁለተኛው ዛፍ ቀበል አደረገና፦ “አንድ ቀን ታላቅ መርከብ ሆኜ መሠራት እወዳለሁ አለ። ብርቱና ውብ መርከብ ሆኜ፥ ነገሥታትንና መኳንንትን በባሕር ላይ ማመላለስ እሻለሁ። ጠንካራ ዛፍ ስለ መሆኔ ከእኔ በተሠራ መርከብ ሲሳፈር ሰው ሁሉ ዋስትና ይሰማዋል። አንድ ቀን ክቡር ዕቃ እሆናለሁ፡” ሲል ምኞቱን ገለጠ።

* * *

ከዚያም ዛፍ ቆራጮቹ፦ እልፍ ብለው ሁለተኛው ዛፍ ዘንድ ደረሱ። አንደኛው ቆራጭ ቀና ብሎ አየና፦ “የህኛው ዛፍ ጠንካራ ይመስላል። የመርከብ ሠሪዎች ቢያገኙት ይገዛሉ” አለና፦መጥረብያውን መዝዞ ዛፉን መቁረጥ ጀመረ። ዛፉም “እሰይ ምኞቴና ፀሎቴ ሊ ፈጸም ነው። ከዚህ ቀጥሎ ታላቅ መርከብ ወደምሆንበት ሥፍራ እወሰዳለሁ” በማለት ደስ አለው።

* * *

ሁለተኛውም ዛፍ ተቆረጠ። ከዚያም ወስደው አንድ ትንሽ የዓሣ ማጥመጃ ጀልባ አድርገው ሠሩት። ዛፉም፦ “ወየው ወየው እኔ የተመኘሁት ታላቅ መርከብ መሆን እንጂ ጀልባ መሆን አልነበረም። ነገሥታትን ን እንጂ፥ ዓሣ አጥማጅን ማመላለስ አልተመኘሁም። እንዲህ ሆኜ ቀረሁ፡” እያለ አዘነ።

* * *

ዓመታት አለፉ። ከዚያም አንድ ቀን፥ ጥቂት ሰዎች ከዛፉ በተሠራው የዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ውስጥ ተሳፍሩ። ከተሳፋሪዎቹም አንዱ፥ ደክሞት ስለ ነበረ ተኛ። ጀልባውም ወደ አንድ ሥፍራ እያመራ ሳለ፥ ታላቅ አውሎ ነፋስ ተነሣባቸው። በዚያን ጊዜ ዛፉ የሰዎቹን ደህንነት ለመጠበቅ አቅም እንደ ሌለው አስተዋለ። ጭንቀትም ሰፈነ። ነገር ግን ሰዎቹ ቶሎ ብለው ተኝቶ የነበረውን ሰውዬ ቀሰቀሱትና አድነን አሉት። ሰውዬውም “…ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ታላቅ ጸጥታም ሆነ። ሰዎቹም ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ።” በዚያን ጊዜ ዛፉ፥ የተሸከመው የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ መሆኑን ተገነዘበ። እግዚአብሔርንም አመሰገነ።

. በመጨረሻም ሦስተኛው ዛፍ የበኩሉን ሲናገር፦ “ከደኑ ሁሉ በላይ ረዥምና ቀጥተኛ ዛፍ ሆኜ ማደግ እሻለሁ። ሰዎችም ወደ ኮረብታው ሲመለከቱ አስቀድመው እኔን ያያሉ። ቀናውን ቁመቴንና የተዋቡትን ቅርንጫፎቼን ተመልክተው እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። በቁመቴ ወደ ሰማይ ቀርቤ እደነቃለሁ። መጥረቢያ ሳይነካኝ ዕድሜዬን እፈጽማለሁ። ከዛፎች ሁሉ ታላቅ ተብዬ እታወሳለሁ።” ሲል ምኞቱን ገለጸ።

* * *

. ከዚያም ዛፍ ቆራጮቹ ወደ ሦስተኛው ዛፍ ደረሱ። ዛፉም ፈራና ተንቀጠቀጠ። ምክንያቱም፥ ከተቆረጠ፥ ምኞቱ ሁሉ ዋጋ ቢስ ሊሆን ነው። ከሁሉ መብለጥ ፈልጓልና። ይሁን እንጂ፥ከዛፍ ቆራጮቹ አንዱ፦ “እኔ ምንም ልዩ ፍላጎት ስለሌለኝ፥ይህ ዛፍ ይበቃኛል” አለና፤ ሦስተኛውን ዛፍ ቆረጠ።

* * *

ሦስተኛውም ዛፍ በትላልቅ ግንዶች ተቆራርጦ፡እዚያው ተተወና፡ ዓመታት አለፉ። ከጊዜውም ርዝመት የተነሣ ዛፎቹ ሁሉ ምኞታቸውን ረሱ።

* * *

ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ሰው መጣና፥ ሦስተኛውን ዛፍ ወሰደው። ሰውዬውም ሕዝቡ እያሾፈበት ፥ በመንደሩ መሐከል እንጨቱን ተሸክሞ፥አለፈ። በኰረብታውም ላይ በደረሰ ጊዜ፥ሰውዬውን በእንጨቱ ላይ ቸነከሩት። ከዚያም፦ ከሩቅ እንደሚታይ እንጨቱን አንሥተው፦ ከተሰቀለው ጋር በኰረብታው ጫፍ ላይ አቆሙት። ሰውየውም በዚያ ሞተ። ሦስት ቀንም ሆነ። በሦስተኛው ቀን ዕሑድ ዕለት፦ የሞተው ሰውዬ ተነሣ። በዚያን ጊዜ ዛፉ ፥ የሆነውን ነገር ማስተዋል ጀመረ። የቆመበት ሥፍራ እንደ ምኞቱ፦ በከተማው ከፍተኛ ቦታ ነበረ፤ ከፍ ብሎ፥ ለሰማይ ቀርቦ፥ ለሁሉ ሊታይ እንደ በቃ አስተዋለ። ነገሥታትን ሳይሆን የነገሥታትን ንጉሥ፥የጌቶችንም ጌታ ለመሸከም እንደ በቃ ተገነዘበ። የሰው ልጆች ሁሉ ለዘለዓለም የሚያስታውሱት ዛፍ ሆነ።

* * *



## የታሪኩ ፍሬ ነገር

ለዘመናት የተመኘነው ቅዱስ ነገር ይኖራል ለጌታ ክብርና ለሰው ጥቅም ብዙ ዕቅድና ዓላማ አድርገን ይሆናል፡፡ ያም እያደር ሲታይ ÷ ከተጠበቀውና ከተመኘነው ጋር ምንም ምስስል የሌለው ሆኖ ይሆናል፡፡ ከዚህ በላይ ባነበብነው ታሪክ እንደ ተመለከትነው:-ዛሬ የደረስንበት ደረጃ የነገራችን ፍጻሜ ይመስል ÷ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊሰማን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ማንኛችንም የመጨረሻው ደረጃችን ላይ እንዳልሆን ማስተዋል እጅግ ይጠቅማል፡፡

የእግዚአብሔርን ክብር በማስቀደም ላይ የተመረኰዙ ፀሎቶችህና ምኞቶችህ አልተቀጩም፡፡ ታምነህ ብትጸና ክብሩና ሽልማትህ በወቅቱ ይገለጻል፡፡ አየህ? የተረክናቸው ዛፎች፡- ሦስቱም የተመኙትን ተቀብለዋል፡፡ የምኞታቸው አመጣጥና ጊዜው ግን እነርሱ ካሰቡት ጋር ምንም አይመሳሰልም፡፡

በመጥረብያ መቆራረጥ÷ በአናጢ እጅ መጠረብ÷ሌሎችን ተሸክሞ ወደሚፈልጉት ማድረስ÷በጐልጐታ በኩል ማለፍና የመሳሰሉት በጉጉት የሚጠበቁ አይደሉም፡፡ እነዚህን በዕቅዳቸው ውስጥ የሚያስገቧቸው አስተዋዮች ብዙ አይደሉም፡፡ የእግዚአብሔር ሃሳብ ከሰው ሃሳብ÷ መንገዱም ከሰው መንገድ እጅግ የተለየ መሆኑን ከቃሉ ብናውቅም በተግባር አናስበውም፡፡ ይሁን እንጂ ከዛፎቹ ታሪክ እንደ ተመለከትነው፡- መልካም ምኞቶችና እንደቃሉ የሆኑ ጸሎቶች በጊዜው ይደርሳሉ፡፡ "በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፡" (ፊልጵስዩስ 1÷6) እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ አይዞህ፡፡ በርታ፡፡



# ጌታ ካለ ሆነ

የለውም መያዣ አይቻልም ያልነው
በጸሎት በፊቱ ወድቀን ስናቀርበው
ሁሉን የሚገዛው እግዚአብሔር ሲያዝዘው
አንድም ነገር ሳይቀር ተችሎ አየነው፡፡

መሳለቂያ አድርገው ጥለው ሲያጥላሉን
በማዋረድ ቃላት ለሌሎች ሲያወጉን
ዲያብሎስም በደስታ እሰይ እሰየው ሲል
እኛም ብለን ነበር የህስ እንዴት ይቻል?

ምሕረቱ ብዙ ነው የእስራኤል አምላክ
እርሱ ፊትን አይቶ አይስትም በሰው መልክ
ቁጣው የዘገየ ምሕረትን የሚወድ
እንደ ቸርነቱ በጽድቁ የሚፈርድ፡፡

ጌታ አምላክ ራርቶልን ከክፉ ሰወረን
ከዲያብሎስ ግሣቱ ከጥርሱ ታደገን
በእግዚአብሔር ብቻ ሕዝቡ እንዲመካ
የጠላት ሃሳቡ ቀርቶ ሳይሳካ
ይኸው በኢየሱስ ስም አለን ተመችቶን
ከቀደመው ይልቅ ምሕረቱ አምሮብን፡፡

በእግዚአብሔር ቅባት ብዙ ተሐድሶ
መንፈሳዊ ፀጋ ጌታ ለእኛ አፍስሶ
ቃሉ እየቀደሰን÷ መንፈስ እያጽናናን
በጌታ ቃል ብርሃን ከጨለማ ርቀን
አንዳች አልከፋንም÷አለን÷ እኛስ አለን
ጌታ ስለ ሆነ የሱስ የተቤዠን፡፡

መላኩ ትዕዛዙ

በመከራ ቀን እግዚአብሔር ይስማህ፤የያዕቆብ አምላክ ስም ያቁምህ፡ ከመቅደሱ ረድኤትን ይላክልህ÷ ከጽዮንም ያጥናህ፡፡ ቁርባንህን ሁሉ ያስብልህ፤ የሚቃጠል መስዋዕትህን ያለምልምልህ፡፡ እንደ ልብህ ይስጥህ÷ ፈቃድህንም ሁሉ ይፈጽምልህ፡፡ በማዳንህ ደስ ይለናል፤ በአምላካችን ስም ከፍ ከፍ እንላለን፤ ልመናህን ሁሉ እግዚአብሔር ይፈጽምልህ፡፡ እግዚአብሔር የቀባውን እንዳዳነው ዛሬ አወቅሁ፤ ከሰማይ መቅደሱ ይመልስለታል፡በቀኙ ብርታት ማዳን፡፡ እነዚያ በሰረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ፤ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን፡፡ እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ ፤ እኛ ግን ተነሣን÷ ጸንተንም ቆምን፡፡ አቤቱ÷ንጉሥን አድነው÷ በጠራንህም ቀን ስማን፡፡ (መዝሙረ ዳዊት 20) አሜን፡፡

# ኢየሱስን መቀበል

ኢየሱስን መቀበል የሚለው አባባል ከመጽሐፍ ቅዱሳችን፡- (የዮሐንስ ወንጌል 1÷11-12) የተወሰደ አባባል ነው፡፡ እርሱም እንዲህ ይላል፡- "የእርሱ ወደ ሆኑት መጣ÷የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፡፡ ለተቀበሉት ሁሉ ግን÷በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤"

ለመሆኑ ኢየሱስን መቀበል ማለት ምን ማለት ነው? ኢየሱስን መቀበል ማለት÷ ከልብ በሆነ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስና ምሕረትን መቀበል ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ከኃጢአተኛ ባሕሪዬ አውጥቶ ሊያጸድቀኝ እንደሚችል በማመን÷ወደ እርሱ መምጣት ነው፡ የደኅንነት ኃይል የሚሆነንን :- መንፈስ ቅዱስን÷ ወደ ልባችን መቀበል ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን መሞቱን በአእምሮ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ÷ በዕምነት ለመቀበል መታዘዝ ነው፡፡ ይህም ረቂቅና ስውር ነገር አይደለም፡፡ የተቀበሉት ሁሉ ልጅነታቸውን ያውቃሉ፡፡ ያለልጅነትም ወራሽነት እንደሌለ እናውቃለን፡፡ ኢየሱስ የልጅነትን ሥልጣን ሰጥቶሃል? አዎን ካልህ :- መቼ?

ምናልባት አሁን በንስሐ ወደ እርሱ መቅረብ ይኖርብህ ይሆን? ምናልባት ይህ ዳብዳቤ ጌታ ያቀደልህ ማሳሰቢያ ይሆን ? አስብበት፡፡ ልብህን መርምር፡፡ ጌታ እንዲህ ይላልና፡- "እነሆ በበር ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን (ልቡን) ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል፤" (የዮሐንስ ራእይ 3÷20) ስለ ጌታ ኢየሱስ በልብህ የሚሰማህ ነገር አለ? ስለ ሲኦልና ስለ መንግሥተ ሰማያት ታስባለህ ? እንደዚህ ያለ ሃሳብ ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ልብ አድርገህ በልብህ የሚሰማህን አድርግ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመሄድ ስሜትህን በቸልታ አታዳፍነው፡፡ እስከዚያው ግን ባለህበት ሥፍራ ተንበርክከህ÷ንስሐ ግባና ተቀበለው፡፡ አስደናቂውንም ማዳኑን ታያለህ፡፡ እኛ የየሱስን አስደናቂነት ያወቅነው ከተቀበልነውና ከገባንበት በኋላ ነው፡፡ያም የእግዚአብሔር አሠራር ነው፡፡ ኢየሱስን በመቀበል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የገባን ሰዎች የፀለይነው ፀሎት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ጌታ ሆይ፡- በግሌ ላውቅህ እሻለሁ፡፡ ስለኃጢአቴ በመስቀል ላይ ስለ ሞትክልኝ አመሰግናለሁ፡፡ ጌታዬና አዳኜ ሆነህ ወደ ሕይወቴ እንድትገባ ልቤን እከፍትልሃለሁ፡፡ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፡፡ ወደ ዘላለም ሕይወት እንድትቀበለኝ÷እንደ ፈቃድህም እንድታበጀኝ እፈቅድልሃለሁ፡፡ ፀሎቴን ስለ ሰማህልኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ አሜን፡፡

# ምስጋና



# ለኢትዮማርት

በሻውኒ ሚሽን ÷ ካንሳስ የሚገኘው ኢትዮማርት ባለቤት፡- አቶ ፈቃዱ እና ቤተሰባቸው ÷ መልዕክታችንን ለማዳረስ ሱቃቸውን ስለ ፈቀዱልን በጣም እናመሰግናለን፡፡ ጌታ ይባርካችሁ፡፡

ኢትዮማርት፡- ምግብ ነክና ባሕላዊ ዕቃዎች÷ወዘተ የሚገኝበት ኢትዮጵያዊ መደብር ነው፡፡ መንፈሳዊ ቴፖችም ያቀርባሉ፡፡

# ....ማሳሰቢያ....

በአሁኑ ጊዜ ወደ አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ (የአረብ ሃገሮች) የምንልካቸው ደብዳቤዎች ቁጥር እየበዛ ነው፡፡ አድራሻዎችና የፖስታ ዋጋ የላካችሁልን ሁሉ ጌታ አትረፍርፎ ይባርካችሁ፡፡

አሁን ግን በቀጥታ ከኢትዮጵያና ከሌሎች የሦስተኛ ሐገሮች÷ አድራሻዎች እየመጡ ስለ ሆነ :- የፖስታ ቴምቤር እጥረት አለብን፡፡

ስለዚህ÷ በዩናይትድ ስቴትስ ያለን አንባቢዎች ችሎታው ስላለ :- የራሳችሁን÷ የፖስታ ቴምቤር በመክፈል እንድትረዱን እንጠይቃለን፡፡ በዓመት 12 ቴምቤር ወይም $4.44USD ብቻ ነው፡፡ "ሃምሣ ሎሚ..." እንደተባለው ማለት ነው፡፡ ይህ አገልግሎት ጠቃሚ ሆኖ ከተሰማችሁና ጌታ ለልባችሁ ከተናገረ በፀሎት÷በምክርና በገንዘብ እንዲሁም በጽሑፍ አስተዋጽዖ ተባበሩን፡፡

ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡
ጌታ ይባርክህ፡፡